# ቅድሚያ ለሚያስፈልገው ጉዳይ ቅድሚያ እንስጥ የ[አዲስ አበባ / ፊንፊኔን] ባለቤትነት በተመለከተ።

**ለውይይት መነሻ:**
በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የህግ አማካሪ
(በሚስጥር የቀረበ)

**መጋቢት 20111**

ሰሞኑን በተለያዩ መድረኮች የአዲስ አበባን ባለቤትነት በተመለከተ ዜጎች ተከፋፍለው ቃላት ሲለዋወጡ ተስተውሏል። ክርክሩና እንካ ስላምቲያው **"የኔ አቋም ብቻ ትክክል ነው"** በሚል መሪህ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ ይህን ጽንፍ የያዘውን ክርክር፣ ጽንፈኞቹ መሰረት አድርገው የሚከራከሩበትን **"ፊንፊኔ የአዲስ አበቤዎች ናት" "ፊንፊኔ የሁሉም ክልሎች ህዝብ ናት" የሚል ሃቅ ላይ ያልተመሰረተ እና ጤናማ ያልሆነ ውይይትን** ወደ ጎን ትቼ የማያከራክሩንን የፌዴራሉንና የክልሉን ሕገ መንግሥት ይዘቶች ብቻ በመመርመር አንዳች ዓይነት መግባባት ላይ እንደርሳለን በሚል እምነት ይህንን አስተያየት ለመሰንዘር ነው። ሕጋዊ መረጃዎች ላይ ያተኮርኩበት ዋናው ምክንያት፣ ሕጋዊ መረጃዎቹ ዛሬ በቀን ተቀን ኑሮአችን የምንጠቀምባቸው ሕያው መረጃዎች በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ **የኢትዮጵያ ታሪክ ብለን እስከ ዛሬ ስንጠቀምባቸው የነበረው የአንዳንድ ብሄሮችን ገድል ብቻ የሚዘክር እንጂ አብዛኛውን የኢትዮጵያን ብሄር ታሪክ በተለይም የኦሮሞዎችን ታሪክ የማያወሳ በመሆኑ፣ ይህንን አግላይ "ታሪካዊ መረጃ" ለክርክር መርቻ ዋቢ አድርጎ ማቅረቡን ስለማላምንበት ነው።**

እኔ: ሁኔታዎችንና ክስተቶችን የማየው በህግ መነጽር ብቻ ነው። በመሆኑም የህገ መንግሥቶቹን ይዘት እንደገባኝ ተርጉሜ አቀርባለሁ። የሰው ልጅ ደግሞ የተለያየ ጭንቅላት ስላለው በአስተሳሰቡም ይለያልና፣ ከፖሊቲካ ግምታዊ ግምገማ ነጻ በሆነ መንገድ **ከኔም ጋር ሆነ ከጠቅላይ ሚኒስትራችን ጋር የማትግባቡበትን ምክንያት ህገ መንግሥቶቹን ብቻ በመመርኮዝ እንድትሞግቱኝ እሻለሁ።**

ያገራችንን ችግሮች በብሄር መነጽር ብቻ አንይ፣ ላለፉት ሰላሳ እና አርባ ዓመታት በጣም ዝቅ ብለናል፣ እስቲ ራሳችንን ከዚያ ከፍ እናደርግና ውይይታችንን ትንሽ እናዘምን ነው። በሃቅ ላይ የተመሰረተ ጤናማ ውይይት ብቻ ነው ላገራችን የሚበጀት። ነገሮችን ሁሉ በጥቁርና ነጭ ቀለም ብቻ መፈረጅ የለብንም። በመሃሉ ግራጫ ቀለም እንዳለ እንረዳ።

"ፊንፊኔ የአዲስ አበቤዎች ናት" "ፊንፊኔ የሁሉም ክልሎች ህዝብ ናት" "ፊንፊኔ የኦሮሞዎች ናት" ወዘተ የሚሉትን መፈክሮችን ስሰማ፣ ይህ **በሌሎች ክልል ዋና ከተሞች የማይከሰት በኦሮሚያ ዋና ከተማ ላይ ብቻ ያተኮረ የባላቤትነት ጥያቄ ምንጩና ዓላማው ምንድነው?** የባህር ዳር ፣ የመቀሌ ፣ የአሶሳና ፣ የጋምቤላ፣ የጂጂጋ ፣ የሃዋሳ ወይም የሃረር ባለቤትነት ጥያቄ አንድም ቀን ሳይነሳ ለምን የአዲስ አበባ ባለቤትነት ጥያቄ ያን ያህል ሊገንን ቻለ? ብዬ ራሴን ደጋግሜ ስጠይቅ መልሱን ለማግኘት ወደ ህገ መንግሥቶቹ አቀናሁ።

ህገ መንግሥት ግን ከፋም ለማም፣ ዜጎች ተስማምተው የሚበጃቸውን ሌላ ህገ መንግሥት እስከሚያጸድቁ ድረስ፣ ዛሬ ጠቀሜታ ላይ ያሉ ህገ መንግሥቶቻችን ብቸኛ መተዳደርያችን ናቸው። መሻሻል አለባቸው ተብሎ ከታመነበት ደግሞ የህገ መንግሥቱን ድንጋጌ ተከትለን የተሻለ ህገ መንግሥት የማናጸድቅበት ምክንያት የለም።

ለአንባቢያን ምቾት ሲባል ከሁለቱም ህገ መንግሥቶች ለዚህ ሙግታችን ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውንና ለጥያቄዎቻችን ተገቢውን መልስ ይሰጣሉ ብዬ የማምንባቸውን አንዳንድ የክልሉንና የፌዴራሉን ህገ መንግሥት አንቀጾች ለይቼ በማስቀመጥ ሙግቴን ልቀጥልበት።

**የፌዴራሉ ህገ መንግሥቱ፣**

- የፌዴራሉ መንግሥት በክልሎች የተዋቀረ ነው
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ አባላት ዘጠኝ ናቸው።

- አንድ የህገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሳብ..... በህዝብ ተወካዮችና የፌዴረሺኑ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛው ድምጽ የደገፈው ከሆነ ለውይይትና ለውሳኔ ለመላው ህዝብና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል።

**የ**ኦሮሚያ **ክል**ል **ህገ መንግሥት፣**

- ኦሮሚኛ የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ይሆናል።
- የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ ከተማ ፊንፊኔ ነው።
- የኦሮሞ ህዝብ የክልሉ መንግሥት የሥልጣን ባለቤት ነው።
- ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የፖሊቲካ ድርጅት፣ ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባላሥልጣኖቻቸው ይህንን ህገ መንግሥት የማስከበርና ለህገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።

በክልላችን የሚኖሩ የሌላ ብሄር ተወላጆች **"የክልሉን የሥራ ቋንቋ እስካወቂ ድረስ በክልሉ መንግሥታዊ ሥራ ውስጥ ተመርጦ ወይም ተመድቦ የመሥራት፣ እንደማንኛውም የክልሉ ተወላጅ ሰርቶ የመኖር፣ ከስፍራ ስፍራ የመዘዋወር፣ ሃብትና ንብረት የማፍራትና የመያዝ"** መብት አላቸው።

**በኔ ግምት፣ የአዲስ አበባን ባላቤትነት አስመልክቶ ዛሬ በመካሄድ ላይ ስላለው መርዘማ ክርክር መንስኤው የፌዴራሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49 እና የኦሮሚያ ክልል ህገ መንግሥት አንቀጽ 6 አለመጣጣም ነው።** ሁለቱም ህገ መንግሥቶች አዲስ አበባን ዋና ከተማዬ ነው ብለው አስቀምጠዋልና! በህገ መንግሥታችን መሰረት ኢትዮጵያ የተዋቀረችዉ በዘጠኝ ክልሎች ነው። በሌላ አነጋገር፣ የኢትዮጵያን ምድር የተከፋፈሏት እነዚህ ዘጠኝ ክልሎች ሲሆኑ ከነዚህ ዘጠኝ ክልሎች ተርፎ ለሌላ ዓላማ የተቀመጠ አንዲት ካሬ ሜትር የኢትዮጵያ ምድር የለም። በመሆኑም፣ የፌዴራሉ መንግሥት፣ ዘጠኙ ክልሎች ከተከፋፈሉት "ይዞታ" ውጪ ነጻና የራሱ የሆነ ልዩ ክልል ወይም ተከልሎ የተሰጠው ቁራጭ መሬት የለውም። ስለዚህ ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ፣ መንግሥታዊ መዋቅርና ቢሮክራሲያዊ አስተዳደር ስናወሳ ስለነዚህ ዘጠኝ ክልሎችና በነዚህ ክልሎች ውስጥ ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንጂ በፌዴራሉ "ክልል" ስለሚኖር ህዝብ አለመሆኑ ግልጽ ነው።

**አንድ የፌዴራሉ አባል የሆነ የክልል ዋና ከተማ እንዴት የፌዴራሉም ዋና ከተማ እንደሆነ ባይገባኝም አንድ ከተማ የፌዴራሉም የክልሉም ዋና ከተማ ሊሆን እንደሚችል አውቃለሁ።** ስለዚህ፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትና የፌዴራሉ መንግሥት ከተስማሙ አዲስ አበባ የሁለቱም ዋና ከተማ የማትሆንበት ምክንያት አይታየኝም።

በተቃራኒው ግን፣ **አዲስ አበባ የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና መሥርያ ቤት ያለበትና የዲፕሎማቲኩ ማህበረሰብ መናኸርያ ስለሆነች የፌዴራሉ መቀመጫ ብቻ መሆን አለባት የሚለውን መሰረተ ቢስ ክስ መቀበል ያዳግታል።**

በተለምዶ አዲስ አበባ የፊውዳሊስት ኢትዮጵያ ዋና ከተማ ስለነበረች ዛሬም ያ አሓዳዊ ሥርዓት ተገርስሶ አገሪቷ በፌዴራሊዝም ሥርዓት መተዳደር ስትጀምርና ኢትዮጵያ በዘጠኝ ራሳቸውን በራሳቸው በሚያስተዳድሩ ክልሎች ስትከፋፈል፣ የፌዴራሉ መንግሥት መቀመጫ መሆኗ ሳይታለም የተፈታ ነገር አድርገው የሚያዩ ወገኖች አሉ። ቢሆን ጥሩ ነበር፣ ዕውኔታው ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው።

በፌዴራሉ ህገ መንግሥት በተደተደነገገው መሰረት ዘጠኙ የፌዴራሉ አካላት የየራሳቸው የሆነ የክልላቸው ርዕሰ ከተማ አላቸው። ባቋቋሙት ክልላዊ ፓርላማና፣ ፓርላማዎቹም ባጸደቋቸው ህጎች ተመርተው ያለፌዴራል መንግሥቱ ጣልቃ ገብነት፣ በርዕሰ ከተሞቻቸው ጭምር፣ ክልላዊ የአስተዳደር መዋቅር ዘርግተው ራሳቸውን ያስተዳድራሉ።

የፌዴራሊዝም ዋና መገለጫውም ይኸው ነውና። የአማራው ክልል በባህር ዳር፣ የትግራይ ክልል ደግሞ በመቀሌ፣ የደቡብ ህዝቦች በሃዋሳ፣ ጉሙዝና ቤኒሻንጉል በአሶሳ ከተሞች ላይ የራስን በራስ የማስተዳደር መብት በተግባር ለመተርጎም የሚረዳ አስተዳደራዊ መዋቅር ዘርግተው የክልላቸውን ነዋሪ ህዝብ መብትና ጥቅም እያስጠበቁ ይገኛሉ።

**በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትም የክልሉ ዋና ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ የራሱን አስተዳደራዊ መዋቅር ዘርግቶ የክልሉ ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም እያስጠበቀ ነው ለዚህም በጥብቅ መሥራት አለበት።**

**በድንሰ ሃሳብ ደረጃ ያልኩት፣ የክልሉን ዋና ከተማ አዲስ አበባን በተመለከተ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት፣ በሌሎች የክልሉ ዞኖችና ወረዳዎች ያለውን ራስን በራስ የማስተዳደር ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣኑን ባግባቡ የተጠቀመበት ስለማይመስለኝ ነው።**

**ለምሳሌ የክልሉ የመሥርያ ቋንቋ የሆነው ኦሮሚኛ ቋንቋ በአዲስ አበባ የመሥርያ ቋንቋ አልሆነም። በሌሎቹ የክልሉ ዞኖችና ወረዳዎች እንደሚያደርገውም፣ በክልሉ ዋና ከተማ በአዲስ አበባ የራሱን አስተዳደራዊ መዋቅርም በሥነ ሥርዓት አልተዘረጋም። ለምን? ዛሬ በወረቀት ደረጃ ያለው "የቃላት" ጥይት የመወራወሩ ጉዳይ ነገ ወደ እውነተኛ ጥይት ወይም ዱላ ሊቀየር ይችላል የሚል ሥጋት አለኝ። ችግሩ ደግሞ በጊዜ ካልተፈታ የባሰ አደጋ ሊያመጣ ይችላል።**

## ታዲያ ምን መደረግ አለበት?

ከዚያ በፊት ግን በህገ መንግሥቱ መሰረት ሥራ ላይ መዋል ያለባቸውና በንትርክና ወከባ ሊቀየሩ የማይችሉ ዕውኔታዎችን ላስቀምጥና ወደ መፍትሄዎቹ ልዝለቅ።

ሀ) **አዲስ አበባ የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ ናት። ከተማዋን ለማስተዳደርም ሆነ የወደፊት ዕጣዋን ለመወሰን የሚችለው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት፣ የኦሮሞ ሕዝብና በክልሉ በህጋዊነት የሚኖሩ ዜጎች ብቻ ነው።** በሃዋሳና በመቀሌ ወይም በአሶሳና በባህር ዳር አስተዳደራዊ መዋቅርና የወደፊት ዕጣ ሌሎችን ክልል እንደማያገባቸው ሁሉ፣ **በአዲስ አበባም ጉዳይ ሌሎችን ክልሎች የሚያገባቸው ሊኖር አይችልም ማለት ነው።**

ለ) የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በሚያካሄዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸውን ሰዎች ሁሉ በመንግሥቱ በቂ ዕርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ ማዘዋወሩ ፍጹም ህጋዊ ነው። በመሆኑም፣ የክልሉ መንግሥት፣ ተፈናቃይ የክልሉን ህዝቦች በራሱ **ፊንፊኔ** መሃል ከተማ ማስፈር ህጋዊ ነው።

የተፈናቀሉ ዜጎችን በተለያዩ የክልሉ አካል የማስፈር ግዴታ፣ አያድርስና ከአዲስ አበባም ሰዎች ቢፈናቀሉ፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ተፈናቃዮቹን ወደ አምቦ ወይም ሻሸመኔ ወስዶ የማስፈር መብትም ግዴታም አለበት ማለት ነው። አለበለዚያ ግን፣ ባንድ በኩል የኢትዮጵያውያንን በማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል በነጻ ተዘዋወረው የመሥራትና የመኖር መብት እንዲጠበቅላቸው እየተሟገትን፣ **የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የጎረቤት አገር ዜጎችን ያሰፈረ ይመስል ይህንንን ሰብዓዊ ድርጊት ለመኮነን መሞከር፣ ወይ የምንፈልገውን የማናውቅና ሰላምና መረጋጋት የሚረብሸን ፣ አለበለዚያ ደግሞ ሌላ ስውር የሆነ የፖሊቲካ ዓላማ ያለን ቡድኖች ነን።**

ሐ) **የፊንፊኔን አስተዳደራዊ መዋቅርንና የክልሉ መሥርያ ቋንቋ የሆነውን ኦሮሚኛና በከተማው ጠቀሜታ ላይ አለማስዋል ችግር ያለው አካሄድ ይመስለኛል። ግን ወደፊት ለሚደረገው ድርድር፣ በከተማው የክልል መሥርያ ቤቶች እንዲሁም በአገሪቷ የመሥርያ ቋንቋ ኦሮሚኛን እንደ አማርኛው ቋንቋ አድርጎ በፌዴራሉ ተቋማት የሥራ ቋንቋ ማድረግ የኦሮሞ ሕዝብ መብት እና የማንንም ዜጋ የማይጥስ ትክክለኛ ውሳኔ ነው።**

መ) **ፊንፊኔ** የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ ስለሆነች በክልሉ ህገ መንግሥት መሰረት ለ**አዲስ አበባ** ከተማ አስተዳደር፣ ከንቲባውንም ጨምሮ፣ ለቦታው ብቁ ነው/ናት ብሉ የሚያስበውን የክልሉን ኗሪ ከየትም የክልሉ አካል አምጥቶ ሊሾም ይችላል። **የሌላ ብሄር ተወላጆችም፣ የክልሉን የመሥርያ ቋንቋ ኦሮሚኛን እስካወቁም ድረስ፣ በከተማዋ ተመድበው ሊያገለግሉ ይችላሉ።**

## ታዲያ መፍትሄው ምን ይሆን?

**አዎ የፌዴራሉ መንግሥት የግድ መቀመጫ ያስፈልገዋል፣ ለዚህ ተብሎ ግን ተከልሎ የተቀመጠ ወይም የተመደበ ቁራጭ የኢትዮጵያ ምድር የለም፣ ስለዚህ ዘጠኙም የፌዴራሉ አባላት ተስማምተው በአስቸኳይ አንዳች ዓይነት ውሳኔ ላይ መድረስ አለባቸው ባይ ነኝ። የተለየ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ያላቸው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በበኩሌ ግን የሚከተሉትን አማራጮች ላቀርብ እወዳለሁ፣**

ሀ) ክልሎቹ በየግላቸው ለፌዴራሉ መቀመጫ የሚሆን የተወሰነ መሬት ከክልላቸው ላይ ቆርሰው መስጠት ይችላሉ።
ለ) ክልሎች በጋራ ተስማማተው ለፌዴራሉ መቀመጫ የሚሆን የተወሰነ መሬት ቆርጠው ሊሰጡ ይችላሉ።

ሐ) **የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ዋና ከተማውን አዲስ አበባን ለፌዴራሉ መንግሥት መቀመጫ ሆኖ እንዲያገለግል ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር ልዩ ውል ሊፈራረም ይችላል**።

**አዲስ አበባ [ፊንፊኔ] የኦሮሚያ ዋና ከተማና የኦሮሞ ህዝብ ደግሞ የክልሉ መንግሥት የበላይ ሥልጣን ባለቤትነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የፌዴራሉ መንግሥት በአዲስ አበባ ላይ ያለውን "ልዩ ጥቅም" እንዲጠበቅለት (ለምሳሌ መሬት ያለ ሊዝ እንዲወስድ፣ የውሃና የመብራት እንዳይከፍል፣ ከሁሉም በተለይ በፌዴራል መሥርያ ቤቶች የመሥርያ ቋንቋው አማርኛን እንደ ኦሮሚኛ እንዲሆን ሊዋዋል ይችላል።**

**መደምደሚያ፣**

**ጠቅላይ ሚኒስትራችንም እንዳሉት** "የአዲስ አበባ [**ፊንፊኔ]** ባለቤትነት ጥያቄ" ባገራችን ሲነሱ ከነበሩና እየተነሱ ካሉ የፖሊቲካ ጥያቄዎች በጣም ለየት ያለ ነው። በመጀመርያ ደረጃ፣ የኢትዮጵያን መሬት በግል ሃብትነት መያዝ እንደማይቻል እየታወቀ **አዲስ አበባን "የኔ ነው" "የኛ ነው" "የአዲስ አበቤዎች" "ወይም "የሁሉም ብሄር ተወላጆች" ነው ብሎ መሞገት ጉንጭ አልፋ ክርክር ይመስለኛል።**

**አዲስ አበባ የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ መሆኗ እየታወቀና የኦሮሞሕዝብና ሌሎች የክልሉ ህጋዊ ኗሪዎች ደግሞ የክልሉ የሥልጣን ባለቤት መሆኑ በህገ መንግሥቱ ውስጥ በግልጽ ተነድፎ እያለ፣ አዲስ አበባ ከዘጠኙ የፌዴራሉ ክልል አባላት በአንዳቸውም ያልተጠቃለለች እንደው በአየር ላይ የተንጠለጠለችና ከክልሎች አስተዳደራዊ መዋቅር ውጪ እንዳለች አስመስሎ ማቅረብና የተለየ ባለቤትነትን መጠየቅ ህገ መንግሥቱን መገዳደር ነው።**

እስከዚያ ድረስ ግን **ወደድነውም ጠላነው፣ አዲስ አበባ የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ ናት። የክልሉ የሥልጣን ባለቤት ደግሞ የኦሮሞ ህዝብና በህጋዊነት በክልሉ የሚኖሩ የሌላ ብሄር ተወላጆች ነው፣ አራት ነጥብ!**

በኔ ግምት፣ አዲስ አበባ የሁለቱም ዋና ከተማ በመሆኗ በውስጧ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሰብዓዊም ሆነ ሀጋዊ መብቶች አልተጣሱም። ያልተገለጡልኝን ደግሞ አጥርቶ የማቅረብ ኃላፊነቱ የናንተ ወገኖቼ ፈንታ ነው። በተረፈ ግን "አፍቃሬ ግጭቶች" የሚያናፍሱትን ወሬ ወደ ጎን ትተን **በፌዴራል ደረጃ በኦፒዲኦ/ኦዴፓ አባልነታችን የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነን መሾሞችን ወቅታዊ ነው። የክልላችን ህዝብም የሚፈልገውና የተደነገገውም ይኸው ነው።**

ውድ ወገኖቼ፣
ቅድሚያ ለሚያስፈልገው ጉዳይ ቅድሚያ እንስጥ። **የታዘብነው የሰብዓዊና ህገ መንግሥታዊ መብት ጥሰት ሳይኖር ዛሬ የአዲስ አበባ "የባለቤትነት" ጥያቄን ማንሳት፣ ከባዱን አገራዊ ችግር ለመጋፈጥ ፈርተን፣ ሌላ ጊዜ በሰላም ሊፈታ የሚቻለውን እዚህ ግባ በማይባል ጉዳይ ላይ ማተኮርና ህዝብን ማነሳሳት ቅንነት የጎደለው ይመስለኛል።** በሁለት ጎረቤት አገሮች መካከል የተነሳ የድንበር ጥያቄ ይመስል የአዲስ አበባን ባለቤትነት ጥያቄ አንስቶ በየሚዲያው ላይ አንጋፋ ዜና አድርጎ ማቅረብና **"አዲስ አበቤዎችን"ና ያካባቢውን ወጣት ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ ለማይኖረው ግጭት ለማነሳሳት መሞከር ወንጀል ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም።** ስለዚህ በጥብቅ እናስብበት፣ አገራዊ ችግሮቻችንን እንደ አንገብጋቢነታቸው በቅደም ተከተል እንደርድርና እነሱን ለመፍታት ጉልበታችንን እናስተባብር።

ፈጣሪ አገሪቷን ይባርክ::

**የጠቅላይ ሚኒስትር የህግ አማካሪ**
**(አዲስ አበባ /ፊንፊኔ) ቢሮ**